# የቀረጥ (ታክስ) ተመላሽ ገንዘብ ብድር
# ተማላሽዎን በከንቱ አይስጡ

**TAX REFUND LOANS**
**DON'T GIVE AWAY YOUR REFUND**

አንዳንድ ቀረጥ አዘጋጆች፡ የቀረጥ ተመላሽ ገንዘብዎን በቶሎ ለመውሰድ የተለያዩ ሃሳቦችን ያቀርባሉ። እነዚህ ያጭር ጊዜ ተመላሽ Rapid Refunds ወይም Refund Anticipation Loans (RALs) የሚባሉ ብድሮች ናቸው። ገንዘብዎን በጥቂት ቀናት እንደሚመለስልዎት ቃል ይገባሉ። የችኮላ ጥሬ ገንዘብ "fast cash" ከመቀበልዎ በፊት የሚከተሉትን አንዳንድ ነገሮች ማወቅ አለብዎት።

ቀረጥዎ ለማዘጋጀ ብድር መውሰድ የለብዎትም። ቀረጥ በነጻ ሊያዘጋጁ ይችላሉ።

የቀረጥ ተመላሽ ብድሮች **ከፍተኛ ወለድና ዋጋ አላቸው!** የሚከተለው፡ በሁለት ሳምንት የሚከፈል የ $1,500.00 ብድር ለማግኘት የሚከፈለው ዋጋ በሶስት መንገድ እናሳያለን።

| | |
|---|---|
| የተመላሽ ገንዘብ ዋጋ | $75.00 |
| የክሬዲት ካርድ የዓመት ወለድ ክፍያ (21%) | $26.00 |
| ከጓደኞችዎ የተበደሩት | $ 0 |

ተማላሹ ከበዛ፡ የማዘጋጅያው ዋጋ ይበዛል!!



የቀረጥ ተመላሽ ብድር ከወሰዱ፡ ትንሽ ገንዘብ ይዘው ይቀራሉ።

| | |
|---|---|
| የቀረጥ ተመላሽ | $1,500.00 |
| የቀረጥ አዘጋጅ ዋጋ | $ -100.00 |
| የቀረጥ ተመላሽ ብድር ዋጋና ወለድ | $ - 75.00 |
| ለርስዎ የሚቀረው ገንዘብ | $1,325.00 |

**ለብድሩ $75 ከፈሉ። በነጻ ለማግኘት የሚችሉትን የቀርጥ ማዘጋጅያ ደግሞ $100 ከፈሉ ማለት ነው።**

ተመላሽ ገንዘብዎ ሌላ ብድሮች ለመክፈል ሊወሰድብዎት ይችላል። ከባንክ ወይም ከሌላ ኩባንያዎች የተበደሩት ገንዘብ ካለ፡ የብድር ፎርም (Refund Loan Form) ከሞሉ፡ አበዳሪዎቹ ተመላሽ ገንዘብዎን ያለብዎት ሌላ ዕዳዎችን መክፈያ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። **የብድር ፎርም መፈረም፡ አለ ተመላሽ ሊያስቀርዎት ይችላል።**

አይ-አር-ኤስ (IRS) በያመቱ አንዳንድ የቀረጥ ተመላሽ ሰነዶችን ይመረምራል።
የርስዎ ለማየት ከፈለገ፡ ተመላሽዎ ለተወሰነ ጊዜ በአይ-አር-ኤስ ይያዛል። ብድር የሰጠዎት ኩባንያ፡ አይ-አር-ኤስ የርስዎ ተመላሽ ሰነድ አይቶ እስኪጨርስ ድረስ አይከፈለውም፤ ስለዚህ ያበደርዎት ኩባንያ ተጨማሪ ወለድ ያስከፍልዎታል።

## ተመላሼ በሙሉ፣ ቶሎና በነጻ እንዴት ለማግኘት እችላለሁ?

የቀረጥ ተመላሽዎ በነጻ ያዘጋጁ። ፈቃደኛ የገቢ ቀረጥ እርዳታ የሚሰጥ፤ ቪታ (VITA) የሚባል ድርጅት፡ በቀረጥ ወራት በሚነሶታ፡ ቢሮዎቹ፡ በየቦታው ክፍት ናቸው። ቀረጥዎችዎ በነጻ ያዘጋጁልዎታል። አንዳንድ ቢሮዎች፡ የቀረጥ ተመላሽዎን በኮምፕዩተር ይሞሉልዎታል። ባካባቢዎ የቪታ (VITA) ቢሮዎች ለማወቅ ከፈለጉ፡ በዩናይትድ ወይ (United Way) በ 211 ለስቴቱ በሙሉ፤ ለመንታ ከተሞች ደግሞ በ (651) 297-3724 ደውለው ይጠይቁ።

አይ-አር-ኤስ (IRS) ተመላሽዎን በቀጥታ ወደ ባንክዎ እንዲያስተላልፍ ያድርጉ። በኮምፕዩተር ከሞሉ፡ በሁለት ሳምንት ውስጥ፡ ወደ ባንክዎ ሊተላለፍ ይችላል። በፖስታ ቤት ከላኩት ደግሞ አራት ሳምንታት ይወስዳል። እንድያውም፤ የስቴቱ ተመላሽ ከዛ በፈጠነ ጊዜ ሊተላለፍ ይችላሉ።

## ቀረጥ የሚያዘጋጅልዎት፡ ሕግን እንዲከተል ያረጋግጡ።

**ብድር የሚሸጡ ቀረጥ አዘጋጆች (እርስዎ ባይገዙም) የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው፤**



- ቀረጥ ተመላሽዎን ቶሎ እንድያዘጋጁ፡
- እንዲፈርሙ ሳይጠየቁ፡ አስቀድመው ፎርሞቹን ይምሉ፡
- በቀረጥ ተመላሹ ዋና ወረቀት ላይ ይፈርሙ፡
- የቀረጥ ተመላሽዎን ቅጂ መስጠት አለባቸው፡
- የተመላሽዎ ቅጂ ላራት ዓመት ማስቀመጥ አለባቸው፡
- ማስረጃዎ በምስጢር መያዝ አለባቸው፡
- በአገልግሎታቸውና ዋጋቸው ቅን መሆን አለባቸው፡
- የተመላሽ ብድር ባይከፍሉም፡ ቀረጥዎን ማዘጋጀት አለባቸው፡
- ቀረጥ ከመክፈልዎ በፊት የሚያደርጉት ቅናሽና ከከፈሉት ቀረጥ ለማስመለስ የሚየደርጉት ተቀናሽ፡ ተገቢና እውነት መሆን አለበት፡
- እንደ W2 የመሰሉ ሰነዶች ሲጠየቁ፡ መስጠት አለባቸው፡
- የሚይስከፍልዎት ዋጋ ከተመላሹ መቶኛ ሳይሆን፡ የተወሰነ መሆን አለበት።

የተመላሽ ብድር የሚሰጡ ቀረጥ አዘጋጆች፡ በያመቱ የሚከፈለው መቶኛ ግምት፤ ተመላሽዎ በስንት እንደሚቀንስና ብድር ሳይወስዱ ተመላሽዎን ለማግኘት የሚወስደው ጊዜ የሚነግር የጽሁፍ ማስረጃ ፎሩም መስጠት አለበት። ተመላሽዎ ከዘገየ የሚከፈል ወለድ ካለ፡ አስቀድመው ማስጠንቀቅ አለባቸው። **እርስዎና ቀረጥ አዝጋጁ፡ ይህ ማስተንቀቅያ መፈረም አለባቹህ።**

ቀረጥ አዘጋጁ፤

- ተመላሹ ለማግኘት፡
- በኮምፕዩተር ለሞምላት፡
- ስለ ተመላሽ ብድር (ከወሰዱ)።

የሚያስከፍለውን ዋጋ ዝርዝር መስጠት አለበት።

ቀረጥ አዘጋጅዎ፤ እነዚህ ሕጎችን ካልተከተለ፡ ለሚነሶታ ቀረጥ ክፍል (Minnesota Department of Revenue) ማመልከት አለብዎት። ፍርድ ቤትም ለመውሰድ ይችላሉ። ጉዳይዎን ካሸነፉ፡ ቀረጥ አዘጋጅዎ የጠበቃውን ዋጋ ይከፍላል። ትንሽ ገቢ ካልዎት ወደ (612) 334-5970 ወይም 1-(800) 292-4150 ይደውሉ።

---

*Minneapolis Legal Aid – CLE*
*MN Legal Services Coalition*
*2324 University Avenue, Suite 101B*
*Minneapolis, MN 55411*

*ይህ ማብራርያ ወረቀት አንድ ዓመት ካለፈው አይጠቀሙበት። የማብራርያ ወረቀቶች ዝርዝር፣ የተሻሻለ ወይም የተቀየረ ሌላ ዘዴ ከፈለጉ ይጻፉልን። የማብራርያ ወረቀቶች፣ ለሕግ ችግሮች ሙሉ መፍትሔ ስላልሆኑ፣ ጠበቃ ያማክሩ።*

© 2011 Mid-Minnesota Legal Assistance. This document may be reproduced and used for non-commercial personal and educational purposes only. All other rights reserved. This notice must remain on all copies. Reproduction, distribution, and use for commercial purposes are strictly prohibited.